### *ዘመነኛውን ሐዋርያነት*

# እናክብረው *ወይስ* እንቅበረው?

## *ታሪካዊ ቅኝት*

***ከተስፋዬ ሮበሌ***

**ወርኀ ጥቅምት 2002 ዓ.ም**

ጠቢብ እምጠቢባን ንጉሥ ሰሎሞን፣ “ጥበብ ከቀይ ዕንቍ ትበልጣለችና፤ የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም” ይላል። ጥበብና ዕውቀት የሌለው ሕይወት ደግሞ በጨለማ የተሸፈነ ዱር ነው። ግእዛውያን፣ “ሰዎች ነባብያን ወንቍኃን ናቸው” ሲሉ፣ እውነቱን ከውሸት ሠናዩን ከእኩይ የመለየት ዐቅም አላቸው ማለታቸውም አይደል? ታዲያ ይህ እጅግ ትልቅ የሆነ ችሮታ የተለገሰው የሰው ልጅ፣ እንደ ደመ ነፍሳውያኑ እንስሳት በዋል ፈሰስ ቢኖር እጅግ ያሳዝናል። ለዚህም ነው ታለቁ ግሪካዊ ፈላስፋ ሳቅራጥስ፣ “ያልተመረመረን ሕይወት ሊኖሩት አይገባም” ያለው። እውነቱን ነው ያልተመረመረን ሕይወት ከመኖር ሞት ይሻላል!!!

ክርስትና አፍቃሬ እውነት ነው። ክርስትና እውነትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ምክንዩአዊ በሆነ መንገድ በማብራራት እውነትን በፍቅር የሚያበሥር ጨዋ ሃይማኖት ነው። ነፍጥም ሆነ እሰጣገባ የክርስትና መለያ ባሕርያት አይደሉም፤ የሚጸየፋቸው እንጂ። ስለዚህ ክርስትና ስለ እውነት ሲሟገት እንዲያው በጭፍን አይሟገትም፤ ምክንያታዊ ማስረጃዎችን ከቃለ እግዚአብሔር፣ ከታሪክና ከአመክንዮ በማጣቀስ በፍቅር እያዋዛ እንጂ። አእምሮን የሰጠን አምላክ አእምሮን ጥለን መርከብ በንፋስ እንደሚገፋ በሃይማኖት ጉዳይ ወዲያ ወዲህ እንድንዋልል አይፈልግም። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ወቅት ለደቀ መዛሙርቱ:— “ገና አልተመለከታችሁምን? አላስተዋላችሁምን? ትዝስ አይላችሁምን?” ብሎ ነበር (ማርቆስ 8÷17-18) አእምሮን ትተው እንዲያው በስሜት የሚክነፈነፉትን አይ ለማለት። እንግዲያው ጸሎታችን እንደ ቤርያ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን እየመረመርን ቃሉን በሙሉ ፈቃድ እንድንቀበል ይሁን (ሐሥ 17÷11)።

ቅዱሳት መጻሕፍት ሥነ ምግባራዊ አካሄዶችንም ሆነ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ያለ አንዳች ማመንታት እውነተኝነታቸውን ባለማሳለስ መመርመር እንደሚገባን አበክረው ያስገነዝቡናል (ዘዳግም 13÷1-5፤ 18÷20-22፤ ሐዋርያት ሥራ 17÷11፤ 2ጴጥሮስ 2÷1፤ 3÷2፤ 1ዮሐንስ 4÷1-2፤ ይሁዳ 17)። አሳዛኙ ጉዳይ ይህን አምላካዊ ትእዛዝ ከሙሉ ልብ ተግባራዊ እንዳናደርገው ልባችንን ሸብበው አፋችንን ለጕመው የሚይዙ ዘመን ያፈጁ በርካታ ጋሪጣዎች ዛሬም አብረውን መኖራቸው ነው:— “አንተ ማን ነህና ነው በሌላው ምግባር ላይ አስተያየት የምትሰጠው?”፣ “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅግን አታንሣ!”፣ “እኔ የምሄድበት የሕይወት አካሄድ ወይም የማስተምረው ትምህርት መንፈሳዊነቱ እጅግ ጥልቅ ስለሆነ፣ የትምህርቴ ጭብጥ ግራ ካጋባህ መንፈሳዊ ብስለት እስክታገኝ ጠብቅ እንጂ፣ አሉታዊ አስተያየት እሰጣለሁ እንዳትል—አልያ ትልቅ መቅሠፍት ይጠብቅሃል!” ወዘተ። እነዚህ የአትመርምሩ ክልከላዎች ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊና ምክንያታዊ ናቸው የሚለውን ጉዳይ እግዚአብሔር ቢፈቅድ በቀጣዩ ጊዜ የምመለከታቸው ቢሆንም፣ ይህን መሰል ክልከላ ተገን በማድረግ፣ ክርስቶስ የሰጠንን የመመርመር ፈቃድ ተከርቸም የሚያስገቡ ተረታተረቶችን ግን ክላ/ወግድ ማለት ተገቢ ነው። ወገኖች ዐርነታችንን ከሚሰልቡ ራሳችንን እንጠብቅ!

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ አንድ ሥጋት ግን አለኝ። ይኸውም ባለፉት ጊዜያት በተለያየ ርእሰ ጉዳይ ላይ፣ “ወገኖች ይህ አስተምህሮ እኮ ትክክል አይደለም፤ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ሁሉ ፍጹማዊ መለኪያ በሆነው በቃለ እግዚአብሔር መመዘን አለባቸው” ያሉ ሰዎች፣ በርካታ አሉታዊ ታርጋ (“የተቀቡ አገልጋዮች ጣላት”፣ “የቅዱሱ መንፈስ ባላንጣ” ወይም “የእግዚአብሔር ቃል ተቃዋሚ”) ተለጥፎባቸው በአንድ ጊዜ በድምፅ ብልጫ “ከቋሚ ተሰላፊነት” “ተጠባባቂ ወንበር ሳይነካቸው” ወደ “ተመልካችነት” ተቀይረዋል፤ ይህ መቼም “ከጫወታ ውጪ” ከመሆንም የከፋ ነው። ጻድቅ ፈራጅ ብድራታቸውን እንደሚከፍላቸው ግን ጥርጥር የለውም። ምናልባት እኔ ይህን ሁሉ ያልሁት ይህ ዕጣ ፈንታ እንዳይደርስብኝ ሠግቼ ቢሆን ይፈረድብኛል? ይህ ዐይነቱ ፍርሓት ቢያድርብኝ ሊፈረድብኝ የሚገባ አይመስለኝም። በአገራችን በኢትዮጵያ በርካታ ክርስቲያኖች በአስተምህሮ ጉዳይ ላይ ወደ አንድ ድምዳሜ

የሚደርሱት ርእሰ ጉዳዩን በቅጡ በመመርመር ሳይሆን፣ “ተቀብቷል” የሚሏቸው ግለሰቦች የሚሰጡትን አስተያየት ተሞርክዘው ነውና።

ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት የተነሣሁት፣ ከእኔ አመለካከት ጋር ተቃራኒ አተያይ ያላቸውን ሰዎች ለማሳጣት ወይም ከእነርሱ ይልቅ እኔ ርቱዕ አቋም እንዳለኝ ለማሳየት በሚሻ መንፈስ አይደለም (ይህን ማድረግ በራሱ ክፋት ባይኖረውም፣ ዐላማዬ ግን ይህ አይደለም ለማለት ነው)። የዚህ ጽሑፍ ቀዳማይ ዐላማ የቃለ እግዚአብሔርን እውነት በፍቅር መግለጥ ብቻ ነው (ኤፌሶን 4÷15)። በተለይ፣ “ሐዋርያት አሉ ወይስ የሉም?” የሚለው ርእሰ ጉዳይ እስካሁን ሲሠራበት የቆየውን የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ተዋረድ አካሄድ የመቀየር እንዲሁም በክርስቲያናዊ አስተምህሮ ሥልጣናዊ መሠረት ከየት ይቀዳል በሚለው ጉዳይ ላይ ትልቅ ተጽእኖ የሚያስከትል ነው።

የመጽሔት ገጽ ውስን በመሆኑ ምክንያት ነገረ መለኮታዊውን ትንታኔ በዚህ ዕትም አላቀርብም፤ በቀጣዩ ዕትም ግን በሰፊው እተችበታለሁ (በርካታ ጊዜያት በነገረ መለኮቱ ዙሪያ የተለያዩ ጽሑፎችን ባቀርብም፣ በቅርቡ ግን ጥንፍፍና ጥልል ያለ ሥራ ይገኘ እንደምቀርብ መግለጽ ፈልጋለሁ—ጌታ ፈቃዱ ቢሆን)። ዛሬ ይህ አስተምህሮ በታሪክ ያለው ስፍራ ምን ይመስላል? ወደ አገራችን የገባው መቼና እንዴት ነው? “ዛሬ ሐዋርያት አሉ” የሚሉ ሰዎች የሚሉትን ያህል ይህ ትምህርት አንገብጋቢ ጉዳይ ከሆነ፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በተለይም ደግሞ ከዘመነ ተሐድሶ በኋላ ያለው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ትምህርቱ ስሕተት ነው ለምን አሉ? ወዘተ የሚሉትን ጉዳዮች በወፍ በረርም እንኳ ቢሆን ለማሳየት ሙከራ አደርጋለሁ።

## የአስተምህሮው ታሪካዊ ዳራ

በዚህ ዘመን የምንኖር ክርስቲያኖች ድንገት እንደ እንጉዳይ በአንድ ጀንበር የበቀልን ከቀድሞዎቹ ጋር አንዳችም ቊርኝት የሌለን ሰዎች አይደለንም። ከቀድሞዎቹ የእምነት አበው ጋር ጥብቅ ትስስር ያለን ነን። በተለይ ክርስትና በዚህ ረገድ ከሁለት ሺህ ዓመት በላይ የሚሆን የዳበረ ታሪክ ያለው ተቋም ነው። በብዙ ነገር ከእኛ ቀዳሚ የሆኑ ሰዎች በርእሰ ጉዳዩ ላይ ምን ብለው እንደ ጻፉ ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንቃኝ ብዙ ትምህርት እናገኛለን። ቃለ እግዚአብሔርንና ታሪክን ማዕከል በማድረግ የመሞገቴም ምክንያት ይኸው ነው፤ ትምህርቱ እነዚህን ሁለት ሥልጣናዊ ምንጮች በእማኝነት ስለሚያጣቅስ እንዲሁም የሚናገር ሁሉ እንደ ቃለ እግዚአብሔር መናገር ስላለበት ነው። ጥንቁቅ፣ ሚዛናዊና ተጠያቂነት ያለበትን ሥራ ማቅረብ ዐላማዬ ቢሆንም፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ የሚያወዛግቡትን ምንባቦች በተመለከተ የምሰጠው ሐቲታዊም ሆነ ታሪካዊ ብያኔ (exegetical and historical decision) ፍትሓዊነት ይጐድለዋል ልባል ግን እችላለሁ (ምንም እንኳ ዛሬ ታሪካዊውን ጉዳይ ብቻ የማነሣ ቢሆንም)። ከፍ ሲል እንደገለጽሁት ዐላማዬ ግልጽ ነው ይኸውም እውነትን በፍቅር መናገር። ሐቲታዊና ታሪካዊ ብያኔዬ መዛባቱ በተጨባጭ ከተነገረኝ እታረማለሁ። እግዚአብሔርን ማገልገል ቃሉን ማገልገል ነውና። በዚህ መንፈስ ወደ ታሪካዊው ትንታኔ እንዝለቅ:—

“ዛሬ ሐዋርያት አሉ” የሚለው አስተምህሮ ትምህርት ቀማሪዎች ትምህርታቸው ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት ወዲህ የተገኘ አዲስ መገለጥ እንደ ሆነ ቢናገሩም በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተነሣው የዘመነ ተሐድሶ እንቅስቃሴ መሪዎች ክፉኛ የተወገዘ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው። ምናልባት አንዳንድ አንባብያን፣ “‘ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት ወዲህ የተገኘ ትምህርት ነው’ እያልህ መልሰህ ‘በዘመነ ተሐድሶ የተወገዘ ትምህርት ነው’ የምትለው ጉዳይ እርስ በርሱ ይጋጫላል” የሚል አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ—ዘመነ ተሐድሶ (Protestant Reformation) ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት በፊት ሳይሆን ከአምስት መቶ ዓመት በፊት የተከሠተ ክሥተት በመሆኑ። አግባብነት ያለው ጥያቄ ነው፤ ምን ማለቴ እንደ ሆነ ላብራራ። የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን (የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን) እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ሊቃነ ጳጳሳቱ፣ ከጴጥሮስ ሐዋርያዊ ሹመት ሲወርድ ሲባረድ የመጣ ሐዋርያዊ ሹመት ባለቤት ናቸው፤ ከዚህም የተነሣ ሊቃነ ጳጳሳቱ ከቀኖናው/ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ናቸው ተብሎ ይታመናል (ይህም ማለት መጽሐፍ ቅዱስን ትርጒም የመወሰን፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተምህሮ የመለወጥ ትውፊት የማሻሻል ወዘተ ሙሉ ሥልጣን አላቸው ማለት ነው)። ከዚህም በተጨማሪ ሊቃነ ጳጳሳቱ በክርስቶስና በአማኙ ማኅበረሰብ መካከል የተቀመጡ ካህን ናቸው (ይፈታሉ፤ ያሥራሉ። እርሳቸው የፈቱት ይፈታል፤ እርሳቸው ያሰሩትም ይታሰራል። ክርስቶስ ለጴጥሮስ የሰጠው የመፍታትና የማሰር ቊልፍ በእጃቸው ነውና ማቴዎስ 16÷16-18)።

በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተነሡት መራሕያነ ተሐድሶዎች፣ ይህ የሐዋርያነት ትኪ (Apostolic succession) አስተምህሮ ማዕከል የሚያደርገው ቃለ እግዚአብሔርን ሳይሆን

ሰውን (ሊቃነ ጳጳሳቱን) ነው፡፡ የሰው ልጆች ሁሉ አስተምህሮአቸውና ምግባራቸው የሚመዘነው በቀኖናዊ መጽሐፍት አንጻር ብቻ ነው የሚል ትምህርት ይዘው ተነሡ (ይህ የተሐድሶ መሪዎቹ አስተምህሮ፣ በላቲን *“ሶላ ስክሪብቹራ”* በመባል የታወቃል)፡፡ መራሕያነ ተሐድሶዎች ይህን ትምህርት ለመቃወም ምክንያት የሆናቸው የሚከተሉት አራት ምክንያቶች ናቸው:— (1) “አማኞች ሁሉ ካህናት ናቸው” (priesthood of all believers) የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ በዚህ ትምህርት ስለሚገረሠሥ፣ (2) ቃለ እግዚአብሔር “ዛሬ ሐዋርያት አሉ” የሚል ትምህርት ስለማያስተምር፣ (3) “ዛሬ ሐዋርያት አሉ” የሚለው ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊ ቃልነት የሚያዋርድ መሆኑ፣ (4) ይህ “የሐዋርያነት ትኪ” ትምህርት መሠረት ያደረገው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያኒቱን በበርካታ ችግሮች ውስጥ መክተቱ (የሥልጣን መሠረት ቃሉ ሳይሆን ግለሰቦች ሆኑ፤ አማኞች ከክርስቶስ ጋር ኅብረት የሚያደርጉት በካህናቱ እርዳታ አማካይነት ሆነ፤ ካህኑ ያሻውን ነገር ቢያደርግ የፈለገውን ነገር ቢያስተምር ሃይ የሚል ሰው ወይም አሠራር ጠፋ)፡፡ የተሐድሶ መሪዎቹ ለእነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉ በርካታ ችግሮች ቀንዳኛ ምክንያት ነው ብለው ያሰቡት “የሐዋርያነት ትኪ” (Apostolic succession) በማባል የሚጠራውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት ነው፡፡

**መ**ራሕያነ ተሐድሶዎች ቃለ እግዚአብሔርን በመጥቀስ የተቃወሙት ትምህርት “የሐዋርያነት ትኪ” (Apostolic succession) እንጂ ከሃያ ዓመት ወዲህ በአንዳንድ መምህራን እየተሰጠ ያለው “ዛሬ የሐዋርያነት ስጦታ/አንብሮተ ዕድ (Apostolic appointment) አለ” የሚለው ትምህርት አይደለም፤ ታዲያ አንተ ይህ ትምህርት በዘመነ ተሐድሶ ተወግዟል እንዴት ትላለህ ልባል እችላለሁ፡፡ ተገቢ ጥያቄ ነው፤ እንዳብራራ ይፈቀድልኝ፡፡ የተሐድሶ መሪዎች “የሐዋርያነት ትኪ” (Apostolic succession) የተቃወሙት ከላይ ባየናቸው አራት ዐበይት ምክንያቶች ነው:— [(1) አስተምህሮው የአማኞችን ክህነት መቃወሙ፣ (2) መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ ሐዋርያት አሉ የሚል ትምህርት ያለማስተማሩ፣ (3) አስተምህሮው የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣናዊ ቃልነት ማዋረዱ፣ (4) ቤተ ክርስቲያንን በበርካታ ችግሮች ውስጥ የሚከት መሆኑ])፡፡ ይህ ደግሞ “የሐዋርያነት ትኪ” (Apostolic succession) ብቻ ሳይሆን፣ “ዛሬ የሐዋርያነት ስጦታ አለ” (Apostolic appointment) የሚለውንም ትምህርት የሚያወግዝ ነው፡፡ እንዲያውም የዛሬው፣ “የሐዋርያነት” ትምህርት፣ የተሐድሶ መሪዎች ከተቃወሙትም ትምህርት ይልቅ የከፋ አስተምህሮ ለመሆኑ ኋላ በስፋት የምተችበት ነው፡፡

**“ይ**ህ እውነት ከሆነ ከሃያ ዓመት ወዲህ ባሉት ጊዜያት ይህ ትምህርት በአገራችን እንዴት ሊያንሠራራ ቻለ?” የሚለው ጥያቄ አግባብነት ያለው ተገቢ መልስም ሊፈለግለት የሚገባ ቍልፍ ጥያቄ ነው፡፡ በአገራችንም ሆነ በውጪው ዓለም የዚህ ትምህርት ቀዳማይ ጠንሳሾችም ሆኑ አቀንቃኞች፣ “የእምነት እንቅስቃሴ” በመባል የሚጠራው የሐሰት ትምህርት[1] ቀማሪዎች ናቸው፡፡ በተለይ በኢትዮጵያ ይህ ትምህርት ለመስፋፋቱ ትልቅ ሚና የተጫወቱት[2]:—

**(1)** በኢትዮጵያ የሚገኘው “የክሩሴደር ቤተ ክርስቲያን”[3] መቈርቈር ምክንያት የሆኑትና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለቤተ ክርስቲያኑ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጉ የነበረው ጆን ኤክሀርት (John Eckhardt)፣ **(2)** አክትስ (“ACTS”)[4] በሚል ርእስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ታትሞ ወደ አገራችን የሚገባው መጽሔት፣ **(3)** እንዲሁም የኬኔት ኢ. ሔጌን (Kenneth E. Hagin) መጻሕፍት ናቸው፡፡ ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው፡፡

---

[1] እንደ ሃንክ ሃንግራፍ እንዲሁም ዲ. አር. ማክኮኔል ያሉ በእንቅስቃሴው ላይ ሰፊ ጥናት ያካሄዱ ዐቃቤ እምነቶች፣ እንቅስቃሴው በመናፍቃን ጐራ የሚፈረጅ ነው ሲሉ፣ ሮበርት ቦማን ያሉ የባብያነ መለኮታውያን ደግሞ ትምህርቱ ትልቅ ስሕተት ያለበት ቢሆንም፣ በመናፍቃን ጐራ መፈረጁ ግን ስሕተት ነው ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ የሚከተሉትን መጻሕፍት ይመለከቷል:— Hank Hanegraaff, *Christianity in Crisis.* (Eugene, Ore.: Harvest House, 1993). D. R. McConnell, *A Different Gospel: A Historical and Biblical Analysis of the Modern Faith Movement* (Peabody, Mass.: Hendrickson, 1988). Robert M. Bowman Jr., *The Word Faith Controversy: Understanding the Health and Wealth Gospel.* (Grand Rapids: Baker 2001).

[2] “የእምነት እንቅስቃሴ” በማባል የሚታወቀውን የስሕተት ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ትልቅ ቦታ ያለው መቀመጫውን በናይጄሪያ ያደረገው “የዴቪድ ኦይዲፓ ሊቪንግ ፌዝ ወርልድ አውትሪች” የሚባለው ድርጅት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ብሎ የእንቅስቃሴው ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ የገባው “ስመ ጥር” ናቸው በሚባሉ የውጪ አገር ሰባኪያን በጻፉአቸው መጻሕፍትና እነዚህ ግለሰቦች የሰበኳቸውን ስብከቶች የተለያዩ ሰዎች በአማርኛ ተርጕመውና በካሴት አዘጋጅተው በቀረቧቸው ትምህርቶች አማካይነት ነው፡፡ በተለይ በዘመነ ደርግ ብዙ ክርስቲያኖች ለመንፈሳዊ ዕድገት ትልቅ ተቀሜታ አለው በሚል የእነዚህን ግለሰቦች ስብከትና ትምህርት በጾምና በጸሎት እንዲሁም በምዕላ (በማኅበር ጸሎት) አብዝተው ያነቡና ይሰሙ እንደ ነበር ይታወሳል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ፣ “ከእምነት እንቅስቃሴ” አስተምህሮዎች መኻል አንዱ የሆነው “ዛሬ ሐዋርያት አሉ” የሚለው ትምህርት በስፋት የተሠራጨው ከላይ በተዘረዘሩት መንገዶች ነው፡፡

[3] ይህ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ “የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን” በመባል ይጠራል፡፡

## ኬኔት ሔጌን

አስተምህሮው ወደ ኢትዮጵያ የገባው በእነዚህ ሦስት አቅጣጫዎች ቢሆንም ምንጩ ግን ያው፣ "የእምነት እንቅስቃሴ"[5] ነው። ከዊልያም ኬኒየን ቀጥሎ፣ "የእምነት እንቅስቃሴ" አባት እንደ ሆኑ የሚነገርላቸው ኬኔት ሔጌን፣ በርካታ መጻሕፍቶቻቸው ወደ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው ለንባብ የቀረቡ ሲሆን፣ *"እርሱ ለሰዎች ስጦታን ሰጠ"*[6] በሚል ርእስ የጻፉት መጽሐፍ በአገሪቱ ውስጥ በስፋት ከተሠራጩት የሔጌን መጻሕፍት መካከል አንዱ ነው። እንደ ጕርጕሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 2003 ዓ.ም ላይ ዕልፈተ ሕይወታቸው የተገለጸው ኬኔት ሔጌን (1917—2003 ዓ.ም) ይህን አስተምህሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመስፋፋቱ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ሰው ናቸው ያልሁት ለዚህ ነው። ሐዋርያት ዛሬ እንዳሉ በመሞገቱ ዙሪያ የሚያጠነጥነውና በ1992 ዓ.ም የጻፉት መጽሐፍ በግልጽ እንደሚያስረዳው፣ በ1987 ዓ.ም ሔጌን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሦስት ሰዓት ያህል በቀጥታ እንደ ተገለጠላቸውና "ስለ አምስቱ ጣምራ አገልግሎቶች" ሰፊ ማብራሪያ እንደ ሰጣቸው[7]፣ ኤፌሶን 4÷11ም መብራራት ያለበት ከዚህ "አምላክ አሳየኝ" ከሚሉት ራእይ አንጻር እንደ ሆነ ይገልጻሉ[8]። ስለዚህ እንደ ኬኔት ሔጌን አመለካከት ኤፌሶን 4÷11 መብራራት ያለበት "ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ *ሥጋ* ተገልጦልኝ የክፍሉን ሐሳብ አስረዳኝ" ከሚሉት አንጻር እንጂ፣ ትክክለኛ የሆነውን የቅዱሳት መጻሕፍት ያአፈታት ጥበብ በመጠቀም አይደለም።

እንደ ኬኔት ሔጌን አስተምህሮ፣ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ምጽአት በንቃት መጠበቅ የምትችለው ዛሬ ሐዋርያት መኖር ሲችሉ ብቻ ነው:—

> "የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አካሉ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በቅርቡ እውን ለሚሆነው የእርሱ ምጽአት ዝግጁ የምትሆነው እነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች በክርስቶስ አካል ውስጥ ተገቢ ቦታቸውን መያዝ ሲችሉ ነው"[9]

ሔጌን ይህን ይበሉ እንጂ በእነጴጥሮስ፣ በእነዮሐንስ፣ በእነያዕቆብና በእነጳውሎስ ላይ የነበረው የሐዋርያነት አገልግሎትና *ሥ*ልጣን ዛሬ እንደ ሌለ ያስረዳሉ። ሔጌን ክርስቶስ በቀጥታ በአካለ *ሥጋ* ተገለጠልኝ በሚሉት ግልጠት ውስጥ ኢየሱስ አራት ዐይነት ሐዋርያት እንዳሉ እንደ ነገራቸው ያስረዳሉ ይኸውም:—

1. ኢየሱስ ክርሰቶስ (*ዕብራውያን* 3÷1)
2. *ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት*
3. *እንደ ጳውሎስ ያሉ መሠረታውያን ሐዋርያት*
4. *መሠረታውያን ያልሆኑ ሐዋርያት*[10]

በተራ ቍጥር አራት ውስጥ ባሉ ሐዋርያት ጐራ የሚፈረጁት ሐዋርያት የሚከተሉትን ሦስት አገልግሎት የሚያገለግሉ ናቸው ይኸውም:— ሚስዮናውያን፣ ቤተ ክርስቲያን ተካዮች፣ መጋቢያንና በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ የነበሩ አንዳንድ መልእክቶችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው የሚመጡ ሰዎች

---

[4] ይህ መጽሔት በቀድሞ ጊዜ ራልፍ ማሆኒ (Ralph Mahoney) በሚባሉ ግለሰብ የሚዘጋጅ ሲሆን፣ ከዐሥር ዓመት ወዲህ ግን ፍራንክና ዊንዲ ፓሪሽ (Frank & Wendy Parrish) በሚባሉ ባልና ሚስት የሚዘጋጅ መጽሔት ነው።

[5] ይህ "የእምነት እንቅስቃሴ" አስተምህሮ "የብልጥግና ወንጌል" በመባልም ይታወቃል፤ አስተምህሮው ምድራዊ ንዋይን በተመለከተ ሰፊ ትምህርት ስላለው ነው "የብልጥግና ወንጌል" በሚለው ስያሜ የመጠራቱ ምክንያት። ታዲያ ይህ ምድራዊ ሀብት የሚዛቀው ጠንክሮ በመሥራት ሳይሆን፣ በአዎንታዊ ዐዋጅ ነው። አስተምህሮው አንድ ሰው ያሚሻው ነገር እንደሚሆንለት አጠንክሮ ቢያምን ክጃሎቱ ሁሉ እውን ይሆንለታል የሚል ትምህርት አለው። ይህ የእምነት እንቅስቃሴ ትምህርት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይ ደግሞ "መገለጥ" በሚባለው አገልግሎት ላይ ያመጣው ውጥንቅጥ በቀላሉ የሚነገር አይደለም። በርካታ "የመገለጥ" አገልጋዮች የሚናገሩትን "መልእክት" የሚናገሩት፣ እንዲናገሩ እግዚአብሔር ስላሳያቸው ወይም ስለተናገራቸው ሳይሆን፣ ይሆናል ብለው የሚያምኑትን ነውና። በዚህ ዐይነቱ አካሄድ የግለሰቡ ፍላጎትና የአምላክ መልእክት መቀላቀሉ ነው። በዚህ እንቅስቃሴ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ወንድም ተሾመ ነጋሽ *"እስክመጣ ድረስ"* እንዲሁም ወንድም ግርማዊ ቡሽ፣ *"የእምነት እንቅስቃሴ"* በሚል ርእስ የጻፏቸውን መጻሕፍት ይመለከታል።

[6] Kenneth E. Hagin, *He Gave Gifts Unto Men: A Biblical Perspective of Apostles, Prophets, and Pastors* (Tulsa: Kenneth Hagin Ministries, 1992).

[7] Kenneth E. Hagin, *He Gave Gifts Unto Men: A Biblical Perspective of Apostles, Prophets, and Pastors* (Tulsa: Kenneth Hagin Ministries, 1992), 6-8.

[8] Hagin, *He Gave Gifts unto Men,* preface.

[9] ዝኒ ከማሁ።

[10] ዝኒ ከማሁ፤ 8-16።

ናቸው[11]። ሔገን፣ ስሚዝ ዊግልስዎርዝ የተባሉ የወንጌል አገልጋይ በመጨረሻዎቹ ውስጥ የሚመደቡና "የእውነት ሐዋርያት" በሚለው ጐራ የሚፈረጁ መሠረታውያን ያልሆኑ ሐዋርያት እንደ ሆኑ ያስረዳሉ[12]።

ሔገን፣ በስፋት እየጠቀስሁት ባለው በዚህ መጽሐፋቸው ውስጥ፣ ዛሬ "መሠረታውያን" የሚባሉና የቀድሞዎቹ ሐዋርያት ሊተኩ የሚችሉ ሐዋርያት እንደሌሉ በአንክሮ ያስገነዝባሉ። እነዚህ ቀደምት የክርስቶስ ሐዋርያት ሊተኩ ያልቻሉበት ቀዳማይ ምክንያት ምን እንደ ሆነ የስረዱበት ምክንያት የሚከተለው ነው:— (1) ዛሬ አንድም ሐዋርያ መጽሐፍ ቅዱስ ከገለጠልን መገለጥ ውጪ የሆነ አዲስ መገለጥ ማምጣት ስለማይችል[13]፣ (2) በቤተ ክርስቲያንና በመጋብያን ላይ የበላይ የሆነ በእነዚህም ላይ ሠልጥናለሁ ሊል የሚችል አንድም ሐዋርያ ዛሬ ስለሌለ ነው[14]። እንዲያውም ሔገን ይህን ነጥብ ሲያጐለብቱ፣ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ሐዋርያት እንኳ ሥልጣነ ሐዋርያነታቸውን ተግባራዊ ሲያደርጉ የታየው እነርሱ ራሳቸው በቅርቡ በተከሏት ቤተ ክርስቲያን ላይ ብቻ ነው ባይ ናቸው":—

> "ከመጋብያን ቢሮ ውጪ በቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይ መሆን የሚገባው አካል እንዳለ የሚያስተምር አንዳችም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አላነበብሁም። በሐዲስ ኪዳን አንዳች ስፍራ ላይ ሐዋርያት በመጋብያንና በሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎች ላይ ሲሠለጥኑ አይታይም"[15]

ሔገን "መሠረታውያን" የሚሏቸው ሐዋርያትም ሆኑ "መሠረታውያን ያልሆኑ" ሐዋርያት የሚጋሩት እነዚህ ሐዋርያት ምልክትና ተኣምር በአገልግሎታቸው ውስጥ እውን እንደሚሆኑ ይህም ተኣምራዊ በሆነ መንገድ ክርስቶስ ስለሚገልጥላቸውና ከእርሱ ጋር ካላቸው ጠንካራ ቊርኝት የተነሣ ራእይና ትምህርት ይቀበላሉ የሚል ነው[16]። ተኣምራት ያደረገውን ሰው ሁሉ ሐዋርያ ማለት እንደማይገባም ያስረዳሉ[17]።

የኬኔት ሔገን አስተምህሮ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ተጽእኖ ለማምጣቱ ጥሩ ናሚናዊ ማሳያ የሚሆነው፣ መስከረም 2 ቀን 2002 ዓ.ም የሐዋርያነት በዓለ ሢመታቸው የተካሄደላቸውና "ሐዋርው ዳንኤል መኮንን" በሚል ስያሜ እንዲጠሩ የተበየነላቸው እንዲሁም "በሐዋርያነት ቀባት መመላለስ" የጀመሩት መጋቢ ዳንኤል መኮንን፣ ለበዓለ ሢመታቸው የተሠራጨውን በራሪ ወረቀት በቀጥታ የተቀዳው ከኬኔት ሔገን መጽሐፍ ነው። እንዲያውም በአንዳንድ ርእሰ ጉዳዮች ላይ በበራሪ ጽሑፉ የተላለፈው መልእክት ከኬኔት ሔገንም ትምህርት የከፋ ስሕተት አለበት፤ ለምሳሌ ኬኔት ሔገን "መሠረታውያኑ ሐዋርያት" በዛሬዎቹ ሐዋርያት ሊተኩም ሆነ ሊመሰሉ አይችሉም ቢሉም ለመጋቢ ዳንኤል መኮንን በዓለ ሢመት የተዘጋጀው የጥሪ ካርድ፣ ከፎቶግራፋቸው ግርጌ "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል" የሚል ጽሑፍ ተከትቦበታል፤ እንዲያውም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን "የሐዋርያት ቊልፍ" (Pontiff Key) ከምትለው የቊልፍ ዐይነት ጋር ጥቅሱ ተያይዞ በአንድ ላይ ቀርቦአል[18] (በቅርቡ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር በዚህና ከዚህ ጋር ተዛማጅ በሆኑ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ጽሑፍ ያሠራጫል)። በቅርቡም፣ የኬኔት ሔገን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት፣ አሜሪካን አገር በሚገኙ ኢትዮጵያውያን መጋቢዎች ደጋፍ በኢትዮጵያ ውስጥ የነገረ መለኮት ትምህርት መስጠት ጀምሯል። አስገራሚው ጉዳይ ኬኔት ሔገን ዘመነኞቹ ሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን ላይ መሠልጣን የላቸውም ማለትም አገልጋዮችን መሾምና የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን መቅጠር የእነርሱ ሥራ አይደለም ቢሉም፣ በመጋቢ ዳንኤል መኮንን ሐዋርያነት የምትመራው የወንጌል ብርሃን ቤተ ክርስቲያን ይህን ሥራ እንዲሠሩት በቅርቡ "ሐዋርያ" የተባሉት ዳንኤል መኮንን ናቸው። በመሠረቱ "ሐዋርያ" የሚል ሢመት ከማግኘታቸውም በፊት አገልጋዮችን ሲሾሙና ሲሽሩ መቆየታቸው ከሢመታቸውም በፊት፣ "በሐዋርያነት ቅባት ሲያገለግሉ" እንደ ቆዩ አመላካች ነው።

## ኬኔት ሔገን አስተምህሮ ማጠቃለያና ግምገማ

የኬኔት ሔገንን የሐዋርያ አስተምህሮ በአጭሩ ሰብስብ እናድርገው። (1) ሔገን ዛሬ ሐዋርያት አሉ የሚለውን ትምህርት ያገኙት ቅዱሳት መጻሕፍትን በማጥናት ሳይሆን፣ ኢየሱስ ለሦስት ሰዓት ያህል በአካለ ሥጋ ተገልጦላቸው ኤፌሶን 4÷11 አስመልክቶ ከሰጣቸው ማብራሪያ ነው። (2) ቤተ ክርስቲያን

[11] ዝኒ ከማሁ፤ 27-40።
[12] ዝኒ ከማሁ፤ 36።
[13] ዝኒ ከማሁ፤ 16, 19።
[14] ዝኒ ከማሁ፤ 24።
[15] ዝኒ ከማሁ።
[16] ዝኒ ከማሁ፤ 47-48።
[17] ዝኒ ከማሁ፤ 61-63።
[18] ይህ መቼም "ድንገት የተከሠተ መመሳሰል ነው" የሚባል አይመስለኝም፤ ሆነ ተብሎ የተደረገ እንጂ።

የክርስቶስን ምጽአት በንቃት መጠበቅ የምትችለው ዛሬ ሐዋርያት መኖር ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ (3) በእነጴጥሮስ፣ በእነዮሐንስ፣ በእነያዕቆብና በእነጳውሎስ ላይ የነበረው የሐዋርያነት አገልግሎትና ሥልጣን ዛሬ የለም፡፡ (4) የዛሬዎቹ ሐዋርያት የሥራ ድርሻ የሚከተለው ነው:— ሚስዮናዊነት፣ ቤተ ክርስቲያን መትከል፣ መጋቢነትና "በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ የነበሩ አንዳንድ መልእክቶችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዞ ማምጣት"፡፡ (5) "መሠረታውያኑ ሐዋርያት" በዛሬዎቹ ሐዋርያት ሊተኩ አይችሉም፤ ይኸውም:— ዛሬ አንድም ሐዋርያ መጽሐፍ ቅዱስ ከገለጠልን መገለጥ ውጪ አዲስ መገለጥ ማምጣት ያለመቻሉ አንደኛው ምክንያት ሲሆን፣ በቤተ ክርስቲያንና በመጋብያን ላይ የበላይ የሆነ በእነዚህም ላይ ሠለጥናለሁ ሊል የሚችል አንድም ሐዋርያ ዛሬ ያለመኖሩ ነው (ሔጌን መሠረታውያን የሚሏቸውም ሐዋርያት በአብዛኛው ይህን የማድረግ ሥልጣን እንዳልነበራቸው ያስረዳሉ)፡፡ (6) "መሠረታውያን" የሚሏቸው ሐዋርያትም ሆኑ፣ "መሠረታውያን ያልሆኑ" ሐዋርያት የሚከተሉትን ባሕርያት ይጋራሉ ይኸውም በአገልግሎታቸው ውስጥ ራእይ ምልክትና ተኣምር እውን መሆኑ ነው፡፡

የሔጌንን የሐዋርያት አስተምህሮ <u>እንገምግም፡፡</u> (1) ሔጌን ይህን አስተምህሮ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ተገልጦልኝ ያስተማረኝ ትምህርት ነው የሚለው ጉዳይ ከሦስት ምክንያት አንጻር በጐሪጥ መታየት ያለበት ነው፤ **አንደኛው** ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ በአካለ ሥጋ ለሰዎች የሚገለጠው በዳግም ምጽአቱ ወቅት መዘመነ ፍጻሜ ብቻ እንደ ሆነ በግልጽ ማስተማራቸው፤ **ሁለተኛው ነጥብ፣** በአሁኑ ጊዜ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ሊያየው በማይችል ታላቅ ብርሃን ውስጥ እንደሚገኝ ቅዱሱ መጽሐፍ ስለሚያስረዳ፣ **ሦስተኛ፤** ሰዎች ተገለጠልኝ ወይም አየሁት በሚሉት ራእይ የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ የሚለወጥ ከሆነ፣ "ተገለጠልኝ" በሚል ሒሳብ ልዩ ትምህርት የሚያመጡትን ሰዎች እንዴት ሃይ ማለት ይቻላል? ነባራዊ/ቋሚ አስተምህሮስ ማዋቀር እንዴት ይቻላል? (2) ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ምጽአት በንቃት ለመጠበቅ ዛሬ ሐዋርያት ያስፈለጉበትን ምክንያት ሔጌን አላብራሩም፤ ስለዚህ ለምን ይህን ትምህርት መቀበል እንዳለብን በግልጽ አልተጠቀሰም፡፡ የቃለ እግዚአብሔር ማብራሪያ ያልቀረበለትን ትምህርት ደግሞ፣ "እገሌ" ብለዋል በሚል ሒሳብ ብቻ መቀበል አይጠበቅብንም—መሠረታችን ቃለ እግዚአብሔር ብቻ ነውና፡፡ (3) እንደ ሔጌን አስተምህሮ በእነጴጥሮስ፣ በእነዮሐንስ፣ በእነያዕቆብና በእነጳውሎስ ላይ የነበረው የሐዋርያነት አገልግሎትና ሥልጣን ዛሬ ከሌለ አገልግሎቱን የማያገለግልና አገልግሎቱንም ለማገልገል የሚያበቃ ሥልጣን የሌለው አገልጋይ ምን ይፈይድልናል? (4) የዛሬዎቹ ሚስዮናውያን ቤተ ክርስቲያን ተከላን የሚያካሂዱ ከሆነ፣ መጋብያን የመመገብ ሥራቸውን የሚሠሩ ከሆነ፣ የሐዋርያ አስፈላጊነት እምኑ ላይ ነው? ሔጌን ሐዋርያት ሚስዮናዊነትንና መጋቢነትን አቀናጅተው ይሠራሉ የሚሉ ከሆነ፣ አንዱ አገልግሎታቸው በሌላው ላይ ተጽእኖ በማምጣት በአገልግሎታቸው ፍሬያማ እንዳይን የማያደርግበት ምክንያት ምንድን ነው? በአብዛኛው ሁለቱም በተራራቀ ስፍራ የሚከወኑ ግብሮች በመሆናቸው፡፡ ሔጌን፣ "በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ የነበሩ አንዳንድ መልእክቶችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዞ ማምጣት" የሚለው ትምህርታቸው ግልጽ አይደለም፡፡ ጉዳዩ መጽሐፍ ቅዱስን በማስተማር ላይ የሚያጠነጥን ከሆነ፣ አስተማሪዎች የሚከውኑት ግብር ስለሆነ ሐዋርያት አስፈላጊነታቸው ግልጽ አይደለም፡፡ ቃለ እግዚአብሔርን መደገፊያ በማድረግ ልዩ ትምህርት የሚያመጡልን ከሆነ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ ልዩ ትምህርት የሚያመጡትን ሰዎች እንዳንቀበል አስጠንቅቆናል፡፡ (5) ሔጌን "መሠረታውያኑ ሐዋርያት" በዛሬዎቹ ሐዋርያት ሊተኩ አይችሉም፤ ይኸውም:— ዛሬ አንድም ሐዋርያ መጽሐፍ ቅዱስ ከገለጠልን መገለጥ ውጪ አዲስ መገለጥ ማምጣት አይችልም እንዲሁም በቤተ ክርስቲያንና በመጋብያን ላይ የበላይ የሆነ በእነዚህም ላይ ሠለጥናለሁ ሊል የሚችል አንድም ሐዋርያ ዛሬ የለም የሚለው ትምህርታቸው ይደግ ይመንደግ የሚባል ነው፡፡ በዚህ ረገድ የዘመኑ ሔጌናውያን መምህራቸውን ቃል እንዲሰሙ እንማጠናለን፡፡ (6) "መሠረታውያን" የሚሏቸው ሐዋርያትም ሆኑ፣ "መሠረታውያን ያልሆኑ" ሐዋርያት በአገልግሎታቸው ውስጥ ራእይ ምልክትና ተኣምር እውን ይሆናሉ ብለውናል፤ በዚህ ጉዳይ ተቃውሞ የለኝም፡፡ በግጥ ሆኖ ከሆነ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን (ይህ ሲሆን ግን እኔ በበኵሌ ከመስማት ባለፈ አይቼ አላውቅም)፡፡ ግን ተኣምራትና ራእይ ለምን የሐዋርያነት መለዮ እንደ ሆነ በቃለ እግዚአብሔር የተደገፈ አንዳችም ሙግት አልቀረበም፡፡ በይሁዳ ምትክ የተተካው ማቲያስም ሆነ ለቆሮንቶስና ለገላትያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ ነኝ የሚል መከላከያውን በስፋት ያቀረበው ሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋርያት የመሆናቸው ምልክት ተኣምራትን ማድረግ እንደ ሆነ አልገለጹም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም የሐዋርያነት መስፈርት ተኣምራት ማድረግ ነው አይለንም፡፡

## አክትስ መጽሔት

በአንድ ወቅት "አክትስ" በሚል ስያሜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ታትሞ ከውጪ አገር ወደ ኢትዮጵያ በስፋት ይሠራጭ የነበረ አንድ መንፈሳዊ መጽሔት፣ "ዛሬም ሐዋርያት አሉ" የሚለውን አስተምህሮውን በተለይ ደግሞ፣ "አምስቱ ጣምራ አገልግሎቶች" የሚላቸውን የአገልግሎት ዘርፎች፣ በአምስቱ የእጅ ጣቶች

ተምሳሌነት እያብራራ በተከታታይ ያቀርብ ነበር፡፡ መጽሔቱ የእምነት እንቅስቃሴን ትምህርት በዓለም ሁሉ ለማስፋፋት ይጠቅማል በሚል እሳቤ በየሦስት ወሩ እየታተመ በነጻ የሚሠራጭ መጽሔት ነው፡፡ ከደርግ ውድቀት በኋላ መጽሔቱ በስፋት በኢትዮጵያ ውስጥ መሠራጨት ሲጀምር፣ የመጽሔቱን ይዘት የተመለከቱ አንዳንድ ወገኖች፣ መጽሔቱ ጤናማ እንዳልሆነ ለማሳሰብ ቢሞክሩም ጩኸታቸው ሰሚ በማጣቱ ምክንያት ያለገደብ የተዘራው ዘር፣ ዛሬ የሚታየውን ፍሬ ማፍራት ችሏል፡፡

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው በመጋቢ ዳንኤል መኮንን በዓለ ሢመት በሚካሄድበት ሰሞን፣ “እንወቃቸው” በሚል ርእስ በአቶ ሙሉወርቅ መኩሪያ ተዘጋጅቶ የቀረበው መጽሐፍ[19]፣ ስለሐዋርያት የሚሰጠው ትምህርት በቀጥታ የተወሰደው ከዚህ መጽሔት ነው (መጽሐፉ መረጃዎቹን ከየት እንደ ወሰደ በግርጌ ማስታወሻም ሆነ በዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር ላይ በግልጽ የማስፈር ፍላጎት ባያሳይም እንኳ)፡፡ አስገራሚው ነገር መጽሐፉ መረጃዎችን ብቻ ሳይሆን፣ ሥልዕላዊ መግለጫውንም የወሰደው ከዚሁ መጽሔት ነው—ሐዋርያን በአውራ ጣት፣ ነቢይን በጠቋሚ ጣት፣ ወንጌላዊን በመኻል ጣት፣ እረኛን በቀለበት ጣት አስተማሪን በተንሿ ጣት፡፡ ምናልባት ጸሓፊው “እኔ ሥዕላዊ መግለጫውን ከዚህ መጽሔት አልወሰድሁም፣ ይህን መጽሐፍ ከማዘጋጀቴ በፊት በ1993 ዓ.ም በሕይወት መጽሔት ቊጥር 47 ገጽ 14 ላይ ይህንኑ ጒዳይ አቅርቤዋለሁ” ይሉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አቶ ሙሉወርቅ በዚህ መጽሔት ላይ ከመጻፋቸው ከጥቂት ወራት በፊት አክትስ መጽሔት ይህንኑ ሥዕላዊ መግለጫ ይዞ ወጥቶአል[20]፡፡ እንዲያውም አቶ ሙሉወርቅ በዚያን ወቅት አምስቱ የአገልግሎት ስጦታዎች በሚል ርእስ በሕይወት መጽሔት ላይ በተከታታይ ይጽፉአቸው የነበሩት ጽሑፎች በአብዛኛው በቀጥታ የተወሰዱት ከዚሁ “ከአክትስ” መጽሔት ላይ ነው[21]፡፡ ይኸው ትምህርት እንወቃቸው በሚለው መጽሐፋቸውም ላይ ተካቶ ለንባብ ቀርቦአል፡፡ ጆን ኤክሀርት በኢትዮጵያ በሚገኘው የክሩሴደር ቤተ ክርስቲያን በመገኘት፣ “አምስቱ ያአገልግሎት ስጦታዎች” በሚል በርእሰ የሰጡት ትምህርት፣ ሐዋርያን በአውራ ጣት፣ ነቢይን በጠቋሚ ጣት ወዘተ መስሎ በማቅረብ አስተምህሮውን አብራርተዋል፡፡ ታዲያ አክትስ መጽሔትም ሆነ ጆን ኤክሀርት ይህ ዐይነቱን ሥዕላዊ ገለጻ ከአቶ ሙሉወርቅ ወስደው ነው ማለት ነው? ከዚህ ሐቅ የምንማረው ቊም ነገር “ዛሬ ሐዋርያትን አሉ” የሚለው ትምህርት በቀጥታ የተቀዳው ከእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች መሆኑን ነው፡፡

“አክትስ” መጽሔት፣ ከኬኔት ሔጌን አስተምህሮ በተለየ መልኩ፣ የዘመኑ ሐዋርያት አገልጋዮችን በአጥቢያ ቤተ ክርቲያን ውስጥ እንደሚሾሙ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን ቅጥር የማካሄድ ሥልጣን እንዳላቸው ይገልጻል[22]፡፡ ይህንኑ መጽሔት መሠረት ያደረገው የአቶ ሙሉወርቅ መጽሐፈም የዘመኑ ሐዋርያት ሌሎች አገልጋዮችን የመሾም እንዲሁም “እውነተኛና አስተማማኝ ውሳኔ” የማስተላለፍ ክህሎት እንዳላቸው፣ ይገልጻሉ (ገጽ 146)[23]፡፡

## ጆን ኤክሀርት

ጆን ኤክሀርት “በቺካጎ በሚገኘው የክሩሴደርስ አገልግሎት መጋቢና የበላይ ተቈጣጣሪ ናቸው”፡፡ በዚሁ ርእሰ ጒዳይ ላይ የሚያጠነጥኑ፣ “ወደ ሐዋርያዊ ተልእኮ መዝለቅ” እንዲሁም “ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንና የሐዋርያት መንፈስ” በሚል ርእስ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ቋንቋ የተተረጐሙ ሁለት መጻሕፍት ያላቸው ሲሆን፣ እነዚህን መጻሕፍት አስተርጒሞ ያቀረበው ጆን ኤክሀርት ለመቈርቈሯ ምክንያት የሆኗትና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከፍተኛ የገንዘብ ዕርዳታ ያደርጉላት የነበረችው ቀድሞ

---

[19] ምናልባት ይህ መጽሐፍ ለመጋቢ ዳንኤል መኮንን በዓለ ሢመት በገጸ በረከት የቀረበ እንዲሁም ለሢመታቸው ጥርጊያ መንገድ ለመክፈት ታስቦ የተዘጋጀ መጽሐፍ ሊሆን ይችላል፡፡ የመጽሐፉ ርእስና የወጣበት ወቅት ይህን የሚያመላክት ይመስላል፡፡

[20] *Acts* (International Edition) July/August/September 2001 *The Five Ministry Gifts: The Gifts of the Son* by Frank R. Parrish. ይህንኑ ትምህርት በቅርቡ በጻፉት መጽሐፍ ላይ አካተዋል፡፡

[21] ዝኒ ከማሁ፡፡ አስገራሚው ጒዳይ አቶ ሙሉወርቅ “ዛሬ ሐዋርያት አሉ” ለሚለው ሙግታቸው አንዳችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አለመጥቀሳቸው ብቻ ሳይሆን፣ 188 ገጽ ባለው መጽሐፋቸው ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን የጠቀሱት ዐሥራ አምስት ጊዜ አይሞላም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ አቶ ሙሉወርቅ፣ “ውድ አንባቢያን ሆይ የግል ልምዳችንን ባህላችንንና የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ በሁለተኛው ደረጃ በማድረግ ወደ እግዚአብሔር ቃል እንመለስ” (ገጽ 148) ሲሉ ያበረታቱናል፡፡ ፡

[22] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 18፡፡

[23] በቅርቡ በማሠራጨው ጽሑፍ ላይ በዚህ በአቶ ሙሉወርቅ መኩሪያ መጽሐፍ ላይ ሰፊ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሒስ አቀርባለሁ፡፡

"ክሩሴደር ቤተ ክርስቲያን" አሁን፣ "የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን" ናት። እነዚህ ሁለት የጆን ኤክሀርት መጻሕፍት:—

> "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መለኮታዊ ግቧን ትመታ ዘንድ የሐዋርያት መንፈስና የሐዋርያት ዕይታ ሊኖራት ይገባል። ወይም በሌላ አነጋገር ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መሆን አለባት። ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መለስ ያለው ማናቸውም ነገር ፋይዳ የለውም። በዚህ ዘመን ጌታ እግዚአብሔር የሐዋርያትን አገልግሎት እንደ ገና በማደስ የሐዋርያትን መንፈስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያፈሰሰ ነው"[24]።

ጆን ኤክሀርት፣ "የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ሲሞቱ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ተገለጸው የተካበተው ፍሬና መሠረት ሁሉ ጠፋ እናም ቤተ ክርስቲየን ከአንድ ሺህ ዓመታት ለሚበልጥ ዘመን በጨለማ ውስጥ ቆየች"[25] የሚል አቋም ያላቸው ሲሆን፣ ይህ የእርሳቸው አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን ካለችበት የጨለማ ሕይወት የሚያወጣ እንዲሁም፣ "ሐዋርያት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየተመለሱ መሆኑን የሚያበስር እንደ ሆነ"[26] ያስረዳሉ። ይህ ብቻ አይደለም የጆን ኤክሀርት መጻሕፍት በዚህ ዘመን የሚገኙት ሐዋርያት ከቀድሞዎቹ ሐዋርያት በተሻለ መንገድ የማገልገል ቅባት እንዳላቸው የሚያስረዱ ከመሆኑም በላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውም የሥራ ድርሻ በስፋት ተብራርቶአል። ይኸውም:— መሠረት መጣል፣ አገልጋዮችን መቀባት፣ መሾም፣ ማስማራት፣ ማዘዝ፣ መፍረድ፣ ተሐድሶ ማድረግ፣ አዳዲስ መገለጦችን ማምጣት፣ አባት መሆን፣ ሕግ ማውጣት፣ አብያተ ክርስቲያንን በበላይነት መቈጣጠር[27] ወዘተ። ከዚህ ውስጥ የተወሰኑትን በቀጥታ ልጥቀስ :—

> "መሠረትን መጣል፤ የሐዋርያት ቅባት የመሠረት ቅባት ነው። ሐዋርያት በእግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወት ውስጥ መሠረት በመጣል እየመጡ ላሉት የእግዚአቤር እንቅስቃሴዎች ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋሉ"[28]።
>
> "ማዘዝ፤ ሐዋርያት ሥርዐትንና አስተዳደርን ወደ ቤተ ክርስቲያን ያመጣሉ። የሐዋርያት ቅባት አስተዳዳሪ ቅባት ነው። የእግዚአብሔር ኀይልና ቅባት በተገቢ ሁኔታ ይፈስ ዘንድ አስተዳደር አስፈላጊ ነው"[29]።
>
> "መፍረድ፤ ሐዋርያት መፍረድንና ዕርማትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ያመጣሉ። በሐሰት ትምህርትና በተሳሳተ ባሕርይ ላይ ፍርድና ውሳኔን ይናገራሉ"[30]።
>
> "በበላይነት መቈጣጠር፤ የሐዋርያት ቢሮና ኀላፊነቱ በኪንግ ጀምስ ትርጉም የሐዋ. 1÷20 በኤጲስ ቆጶስ ተመስሏል። ኤጴስ ቆጶስ መሆን ማለት ደግሞ በበላይነት መቈጣጠር ማለት ነው። ሐዋርያት አብያተ ክርስቲያንን በበላይነት ይቈጣጠራሉ"[31]።
>
> "መሾም፤ ሐዋርያት ብዙ አመራርን በስፍራው ያቆማሉ፤ ይሾማሉ፤ ይህም ምርጫንና መጽናትን ያጠቃልላል። የሐዋርያት ሹመት ፍሬያማነትን ያጐናጽፋል" [32]።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ጆን ኤክሀርት ሐዋርያዊ ሥልጣናቸውን በመጠቀም ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ አይመጣም የሚል ትምህርት በማስተማር ላይ ይገኛሉ። "ሐዋርያት መሠረት ጣይ" እስከ ሆነ ድረስ "ይህን መሠረት የማጣል ሙሉ መብት አለው"። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ አዲስ አስተምህሮአቸው ምክንያት በኢትዮጵያ የምትገኘው፣ "የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን" ከእርሳቸው ጋር ያላትን ግንኙነት እንዳቋረጠች ተገልጾአል።

## ማጠቃለያ

"ዛሬ ሐዋርያት አሉ" የሚለው ትምህርት ከእምነት እንቅስቃሴ መምህራን "ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ በቀጥታ ተገልጦላቸው የሰጣቸው" ልዩ መገለጥ ነው። ይህን አካሄድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

---

[24] ጆን ኤክሀርት፤ *ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንና የሐዋርያት መንፈስ፤* መቅድም።

[25] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 25።

[26] ጆን ኤክሀርት፤ *ወደ ሐዋርያዊ ተልእኮ መገለጥ፤* የጀርባ የውጪ ሽፋን።

[27] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 67-70።

[28] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 68።

[29] ዝኒ ከማሁ።

[30] ዝኒ ከማሁ።

[31] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 69።

[32] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 70።

ተፈጻሚ ካደረግነው ሽማግሌዎችን የሚሾመው፣ መጋቢያንን የሚቀባው፣ አብያተ ክርስቲያናትን በበላይነት የሚቈጣጠረው፣ አዳዲስ አስተምህሮዎችን የሚያመጣው "ሐዋርያ" የተባለው ግለሰብ ነው። የሐዋርያውም ተጠሪነት በቀጥታ ለእግዚአብሔር ስለሆነ አንድም ሰው "ይህን ለምን አደርግህ?" ሊለው አይችልም። እንግዲህ ዛሬ "ተቀበሉ" እየተባልን ያለነው የሐዋርያነት ትምህርት ይህ ነው። ታዲያ ይህ አካሄድ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተነሡት የተሐድሶ መሪዎች የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን የሐዋርያነት አስተምህሮ ከተቃወሙበት ትምህርት በምን ይለያል? እነዚህ ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን ራስ በሆነው በኢየሱስና በምዕመናን ጠቅላላ ጉባኤ መኻል የሚገቡ ከሆነ፣ "አማኞች ሁሉ ያላንዳች ካህን በቀጥታ በክርስቶስ ፊት መቅረብ ይችላሉ" የሚለው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነት እንዴት ጸንቶ ሊቆም ይችላል። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ያለው "የርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳት" አካሄድ ከዚህ በምን ይለያል? ውድ የክርስቶስ ቤተ ሰቦች፣ እየመጣብን ያለው አደጋ ብዙዎች ከሚገምቱት በላይ እጅግ ትልቅ ነው። ዛሬ ይህ እኩይ ትምህርት አጥብቀን የማንቃወመው ከሆነ፣ ነገ የምንወዳት ቤተ ክርስቲያን "ሐዋርያት ነን" በሚሉ ደፋሮችና ጥቅመኞች አይሆኑ ሆና ትገነጣጠላለች። ይህ የዘመኑን የሐዋርያነት ትምህርት ግባተ መሬቱ እውን ልናደርግ፣ መጻኢው ትውልድ ይማርበትም ዘንድ ሐውልት ልንሠራበት ይገባል።

ኦ አብ በእንተ ኢየሱስ ርዳአነ፤ ኦጵራቅሊጦስ መንፈስ ጽድቅ ርዳአነ፤ አሜን።